ስም መስገድ ወዘተረፈ ማለት፣ በእርሱ ሥልጣን ሥር መዋቀር፣ በእርሱ ማዕከልነት መደራጀት፣ በእርሱ ጥላ ሥር መጠለል፣ በመጠጊያነቱ ውስጥ ማደር፣ ለእርሱ እምልኮተ ስግደት ማቅረብ፣ እንደ ቃሉ መኖር ወዘተ ማለት ነው። እንግዲያው የእግዚአብሔርን ስም የምንቀድሰው፣ ኑሮአችንንና አስተሳሰባችንን በእርሱ አሳብና ፈቃድ ውስጥ በመክተት እንጂ፣ በአንድ ግብር መጨረሻ ላይ የተጸውዖ ስሙን በመጥራት ወይም ባለመጥራት አይደለም።

አባይ ነባዮች ያሻቸውን አድርገው፣ በድርጊታቸውም መጨረሻ "በኢየሱስ ስም" ማለታቸው፣ ግብራቸውን አያጸድቅም አስተምህሮአቸውን ርቱዕ አያደርገውም። "ኢየሱስ" የሚለው ስም መጠሪያ እንጂ፣ ምትሐታዊ ቀመር አይደለምና።

እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን አባይ ነባዮች "እኔ ኢየሱስ ነኝ" እያሉ በስሙ እንደሚመጡ ጌታ ራሱ ነግሮናል፣ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ…ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" (ማቴ. 24÷4-5:24)። ወገን ስማ—የኢየሱስን ስም የጠራ አባይ ነባይ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ነው ማለት ስሕተት ነው።



# ክፍል ዐሥራ አንድ

## የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን መበራከት ምስጢር ምንድን ነው?



### ሀ. ለምን ሰዎች አባይ ነባዮችን እንዲሁም መናፍቃንን ይከተላሉ?[1]

### አጠቃላይ እሳቤ

የአንድን ክሥተት ትክክለኛ መንሥኤ ማወቅ፣ የመፍትሔው አስተንትኖት ቀዳማይ እርምጃ ነው።

[1] የክፍሉ ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፣ ከሚከተለው መጽሐፍ ነው:— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults* (Grand Rapids: Zondervan, 1995), 81-85.

እንግዲያው ሰዎች አባይ ነብዮችን እንዲሁም መናፍቃንን ለምን እንደሚከተሉ እንመርምር።

## 1. የግል ፍላጎት ምክንያት ሊሆን ይችላል

ወደድንም ጠላንም፣ ማንኛውም ሰው የራሱ የሆነ ፍላጎት አለው—መጠኑና ዐይነቱ ቢለያይም እንኳ። የአዳም ዘር፣ ዐቅሙ በፈቀደ መንገድ ሁሉ፣ እነዚህን ፍላጎቶች ቢሆን በቋሚነት ባይሆን በጊዜያዊነት ለማርካት የተቻለውን ትንቅንቅ ይገጥማል። ሰብአዊ ፍጡር ሊያሟላ የሚፈልገው ትልቅ ፍላጎት እንዳለው፣ ከማንም ይልቅ በውል የተረዱት በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባዮችና መናፍቃን ናቸው።

ይህን የሰው ልጅ ፍላጎት እጅግ ቀላል፣ እጅግ ፈጣን እንዲሁም እጅግ ፍቱን ወይም ዘላቂ በሆነ መንገድ መፍታት የሚያስችል መፍትሔ፣ በእነርሱ እጅ ብቻ እንደሚገኝ አጠንክረው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታ ሰዎች በቀላሉ ወደ አባይ ነባዮችና መናፍቃን እንዲሳቡ ምክንያት ይሆናል። ችግሩ እንዲፈታለት የማይፈልግ ማነው? ችግር በሌለበት ሕይወት ውስጥ መኖር የማይፈልግ ሰብአዊ ፍጡር ማን ነው?

ኩርት ቫን ጎርደን የሚባሉ ስመ ጥር ዐቃቤ እምነት፣ “መናፍቃንን በወንጌል መድረስ” በተባለው መጽሐፋቸው ላይ፣ ሰዎች አባይ ነባዮችንና መናፍቃንን በመከተል ሊያረኳቸው የሚሿቸውን ፍላጎቶች በአራት ከፍል መድበዋቸዋል። ይኸውም:— አእምሮአዊ ፍላጎት፣ ማኅበራዊ ፍላጎት፣ ስሜታዊ ፍላጎትና መንፈሳዊ ፍላጎት ናቸው[2]። ማንኛውም ሰው እነዚህ ፍላጎቶች በተለያየ መጠን

[2] ዝኒ ከማሁ *Kurt van Gorden, "Unity School of Christianity" in Evangelizing the Cults* ገጽ 140 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።



ስላሉት፣ ፍላጎቶቹ በራሳቸው መጥፎ አይደሉም። እነዚህንም ተገቢ ፍላጎቶች በእግዚአብሔር ቃል እውነት ያለማርካት፣ ሰዎች በመናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳቡ ወይም አዲስ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ እንዲጀምሩ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

አባይ ነባዮችና ሉላዊነት *(globalization)* የሚባለው የምጣኔ ሀብት ፍልስፍና፣ በአንድ ሁነኛ መንገድ ይመሳሰሉብኛል። ሉላዊነት አዳዲስ ምርትን ካስተዋወቀ በኋላ፣ ኋላ ምርቱን መጠቀም በሕይወት ለመኖር ወሳኝ ጉዳይ እንደ ሆነ ሰዎች አምነው እንዲኖሩ ያስገድዳል። አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፤ በቀድሞ ጊዜ በአገራችን ኢትዮጵያ ስኳር በጭራሽ አይታወቅም ነበር—ያውም በእኔ ዕድሜ (ዐደራ ዕድሜዬን እንዳልጠየቅ)። ደቾች (የሆላንድ አገር ሰዎች) በመተሐራና በወንጂ የስኳር ፋብሪካዎችን ከፍተው ስኳር ቢያመርቱም፣ ሕዝቡ ግን ለምርቱ አንዳችም ቍብ አልነበረውም። በወቅቱ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብርቅ ስለነበር፣ እነዚህ ድርጅቶች ምርታቸውን ያስተዋውቁ የነበሩት ጥሩንባ ነፊ፣ ነጋሪት ጐሳሚ በየመንደሩ በመነስነስ ነበር።

የእነዚህ ፋብሪካዎችም ሎጎ ዝሆን ነበር—ስኳር እንደ ዝሆን ያፋፋል፣ ያጠነክራል ለማለት ተፈልጎ ይመስለኛል ዝሆን እንዲመረጥ ምክንያት የሆነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገራችን በኢትዮጵያ ውፋሮ፣ እንደ ትልቅ ሰማያዊ በረከት እንደ ልዩ የአምላክ ጸጋ ይታይ ነበር—የዛሬን አያድርገውና።

ከፋብሪካው ግንባታና ከምርታማነቱ ይልቅ፣ የፋብሪካውን ባለሀብቶች ያደከማቸው ስኳርን ለኢትዮጵያውያን ማቅመስ ነበር። ዛሬ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለስኳር መኖር እንዳስቸገረው፣ የስኳር ጉዳይ ትልቅ የፖለቲካ አጀንዳ እንደ ሆነ እየታየ ነው። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ “ስኳር የተወደደው ገበሬው ስኳር ስለቀመሰ፣

ጣዕምናውን ስላጣጣመ እንጂ፣ ምርቱ ስለተጓደለ አይደለም" የሚል መከራከሪያ፣ ፓርላማው ዘንድ ይዘው ቀርበው እንደ ነበር አስታውሳለሁ። እነሆ ዛሬ ስኳር የምኾትና ይጥፍጥና ሁሉ ቀኖና ሆኖ ያገለግላል።

በአንድ ወቅት በዓለማችን፣ ኢንተርኔት/ዋይ ፋይ[3] አገልግሎት አይታወቅም ነበር። ዛሬ የዓለማችን ነዋሪ ሕይወቱ በብዙ ረገድ የተቈራኘው ከዚሁ ዘመን አመጣሹ ኢንተርኔት ጋር ነው። ይኸው ዛሬ ያለተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ያለኢሜል፣ ያለፌስቡክ፣ ያለቴሌቪዥን፣ ያለሬዲዮ መኖር እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ነው። ምናልባትም ያለእነዚህ መኖር የማይቻልበት ዘመን ላይ ደርሰናል ቢባል ግነቱ መጠነኛ ነው። በአንድ ወቅት እነዚህን ነገሮች አንጠቀምም ነበር፤ እንዲያውም መኖራቸውንም አናውቅም ነበር። ዛሬ ግን በዕጸደ ሥጋ ለመኖር ዋነኛ ጉዳዮች ሆነው ቀርበውልናል።

የሉላዊነት የምጣኔ ሀብት ፍልስፍናንና አባይ ነባዮችን የሚያመሳስላቸው፣ በሰው ሕይወት ውስጥ ፍላጎት በመፍጠር እንደ ዋዛ ያስገቡት "ሽቀጥ"፣ ኋላ ያለ እኔ ምድራዊ ህልውና ሊኖራችሁ አይችልም ይላል።

እንደ አንጕዳይ በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባዮች፣ "ትፈወሳለህ...አሜን በል!"፣ "የያዝኸው የረዘዝኸው ሁሉ ይባረካል...ጕንህ ላለው ዐውጅለት!"፣ "በድል ላይ ድል በጸጋ ላይ ጸጋ ትጐናጸፋለህ...የገባው አሜን ይላል!" በሚለው ስብከታቸው በክርስቶስ ትመጣለች የምትባለውን መጻኢ ዘመን፣ አሁኑኑ ከጕናችን ይከሥቷታል። ልክ ነው በግዳጅ ካልሆነ በቀር፣ ከችግር ጋር መኖር ማን ይፈልጋል? ፍላጎቱ ተሟልቶለት አምሮ ደምቆ መኖር ማን ይጠላል? ስለዚህ የአባይ ነባዮች ስብከት የማያማልለው፣

[3] "ዐውደ መረብ" የሚል ስም ወጣለት ልበል?



ዐዋጃቸው ጕምን መጨበጥ፣ መርዝን መጨለጥ እንደ ሆነ የተረዳ "ተራማጅ"[4] ብቻ ነው።

አባይ ነባዮችና የሉላዊነት ፍልስፍና ፍላጎት በመፍጠር ወይም በመጫር ረገድ አንድ ዐይነት ጠባይ ቢኖረውም፣ መፍትሔንና እርካታን በማምጣቱ ረገድ ግን፣ የአባይ ነባዮቹ ስብከት ህልም ነው፤ ቅዠት ነው። አባይ ነባዮችና መናፍቃን የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ለጥቂት ጊዜ ሊያሟሉ ይችሉ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ለችግሮቹ የሚሰጡት መፍትሔ ዘላቂነትም ሆነ እውነተኛነት ሊኖረው አይችልም። ምክንያቱም ለሰዎች ችግር ትክክለኛና ዘላለማዊ መፍትሔ ከሚሰጠው ከእውነተኛው ወንጌል ርቀዋልና። ከዚህም የተነሣ የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ማርካት ይሳናቸዋል። የሰዎችን ፍላጎት ዘላቂ በሆነ መልኩ ማርካት የሚችለውና ጥያቄዎቻቸውን መመለስ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነውና።

ወደድንም ጠላንም፣ ክርስትናም ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት የታመመ ሁሉ ይፈወሳል፣ የተቸገረ ሁሉ ከችግሩ ነጻ ይወጣል፣ ያጣ የነጣ ሁሉ ቱጃር ይሆናል የሚል ትምህርት በጭራሽ የላቸውም[5]። አምላክ ሊፈውሰን፣ ክብሩን በእኛ ሊገልጥ ቢፈልግ የእኛ ነቢያትን ማሳደድ አንዳችም ፋይዳ የለውም። አምላካችን ልዑል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ፈቃዱም እውን እንዳይሆን የሚከለክለው አንዳችም ምክንያት የለም። የአምላክ ልዑላዊ ፈቃድ በአድራሻችን ያገኘናል። ሊፈውሰን ከፈለገ አድራሻችን ሊጠፋው አይችልም። ባይሆን እንኳ የተሻለውን ትንሣኤ ተስፋ በማድረግ ወደ መጻኢው

[4] ያልባነነውን ከ"አድሃሪ" ጋር ለማገናኘት ነው።

[5] ለበለጠ ማብራሪያ፣ "ክርስትና ለጤንነትና ለሀብት ዋስትና አልሰጠም" (ገጽ 197-204) የሚለውን ክፍል ይመለከቷል።

ሕይወት እንሰበሰባለን (ዕብ. 11÷35-40)፡፡ ችግርና ሕማም ቢኖር እንኳ፣ ኀይሌ በድካምህ ይገለጻል፤ ጸጋዬ ይበቃኻል ወዘተ የሚለውን የጀግኖች ሐዋርያትና ነቢያትን እምነት ኖረን፣ በእምነት ጀግነን ልናልፍ እንጂ፣ የአባይ ነባዮች መጫወቻ ልንሆን አይገባም (ዕብ. 11÷35-40፤ ማቴ. 8÷20፤ 1ቆሮ. 4÷9-13፤ 2ቆሮ. 11÷23-27፤ 12÷10፤ ያዕ. 5÷10-11)፡፡

## 2. አስተምህሮ ምክንያት ሊሆን ይችላል

ሰዎች ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ከተረዱ በኋላ፣ የተረዱትን እውነት ትተው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አይገቡም ብሎ ማሰብ አግባብ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በአንጻራዊነት ሲታይ፣ በዚህ መልኩ መናፍቃንን የሚከተሉ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በአሜሪካን አገር በተደረገ አንድ ጥናት መሠረት፣ አብዛኞቹ ሰዎች የሞርሞንን እምነት የሚቀበሉት፣ ሞርሞኖች ምን ዐይነት እምነት እንዳላቸው አስቀድመው ካወቁ በኋላ ነው፡፡

## 3. ቤተ ክርስቲያን ማሟላት ያለባትን ሳታሟላ ስትቀር

ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንድታሟላላቸው የሚፈልጉትን ነገር ተሟልቶ ካላገኙት፣ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ሲጀምሩ አሊያም በተጀመረው እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ሦስት አራተኛ የሚሆኑት የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን አባላት፣ በአንድ ወቅት



የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አባላት የመሆናቸው[6] ጉዳይ፣ ይህንኑ እውነት የሚያጠናክር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያንን በእጅጉ እያሳሰቡ የሚገኙት አብዛኞቹ አባይ ነባዮች ከቤተ ክርስቲያን የወጡ ናቸው፡፡ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀውን የኑፋቄ ድርጅት የመሠረቱት ቢሾፕ ተክለማሪያም ገዛኸኝ በአንድ ወቅት የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ነበሩ፡፡ ነገር ግን አንድ በራሪ ጽሑፍ/ትራክት በማንበብ የድርጅቱን አስተምህሮ እንደ ተቀበሉ እንዲያውም የኑፋቄ ድርጅቱ ፈታውራሪ እንደ ሆኑ ይታወቃል[7]፡፡ "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት መሥራች የነበረውም ቻርልስ ታዝ ራስል በአንድ ወቅት የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን አባል ነበር፡፡

ቫን ባለን መናፍቅነትን፣ "ያልተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ"[8] ብሎ ይጠራዋል፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መሙላት ያቃታትን ባዶነት፣ መናፍቃን እየሞሉ ብዙዎችን በማሳሳት ላይ ስለሚገኙ ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመናፍቃን ቍጥር እየጨመረ መምጣት፣ የቤተ ክርስቲያንን ጕድለት የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን፣ ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን ተዝቢ ፍላጎት ማርካት የምትችለው፣ የምእመናኑ ፍላጎት ሲታከልበት እንደሆነም መዘንጋት የለብንም፤ ቢሆንም ግን ቤተ ክርቲያን የአባሎቿን መንፈሳዊ፣ አእምሮአዊ፣

---

[6] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 152 *Josh Mc Dowell and Don Stewart, Assisted by Kurt Van Gorden The Deceivers.*

[7] ለበለጠ ማብራሪያ የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ፣ "ሰባልዮሳውያን" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ሁለት ቅጽ መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡

[8] ዝኒ ከማሁ ገጽ 152 *Van Baalen, Chaos of the Cults* ገጽ 390 ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡

ማኅበራዊና አካላዊ ፍላጎት እንደ እግዚአብሔር ቃል የማርካት ታላቅ ኀላፊነት አለባት።

ዛሬ ለያዥ ለገራዥ ያስቸገረው የአባይ ነባዮች ጉዳይ፣ በአንድ ጀንበር ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ችግር አይደለም። ለረጅም ዓመታት፣ "ለክፋት አይሰጥም" የሚባሉ ትምህርቶችና አካሄዶች ናቸው ዛሬ ተጠረቃቅመው ድንገት ደራሽ ጉርፍ ሆነው ከተፍ በማለት፣ ቤተ ክርስቲያንን ታዛ አልባ ያደረጓት። ዛሬም ይህ ችግር፣ በአንድ ጀንበር አልባት ያገኛል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው። ቀስ በቀስ እንደገባ፣ ቀስ በቀስ ነው የሚወጣው። በተቀናጀ አኩይ ጥረት እንደ ገባ፣ በተቀናጀ ሠናይ ጥረት ነው የሚወጣው። ለመግባት ጊዜ እንደ ፈጀበት ሁሉ ለመውጣትም ጊዜ ይፈልጋል።

## ለ. ሰዎች አባይ ነባዮችንና መናፍቃንን በመጠጋት ሊያሟሏቸው የሚሹአቸው ፍላጎቶች

### 1. ፍቅር

ሰዎች አባይ ነባዮችንም ሆነ መናፍቃንን ከሚጠጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ፍቅርና ክብካቤ ፍለጋ ነው። ይህን በበቂ ሁኔታ ካገኙ ባገኙባቸው ስፍራዎች እስከ መጨረሻው ለመቆየት ይገደዳሉ። የአባይ ነባይ ተከታዮችንም ሆነ መናፍቃንን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት አዳጋች ከሚያደርጉአቸው ምክንያቶች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ሰዎች፣ "ዩኒቲ ስኩል ኦፍ ክርስቲያኒቲ" በሚባለው መናፍቃዊ ድርጅት እንዲሳቡ የሚያደርጋቸው፣ ድርጅቱ ለፍቅር ከፍተኛ ስፍራ ስለሚሰጥ ነው[9]።

[9] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 153 ከMc Dowell & Stewart, *The Deceivers* ገጽ 18 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።



### 2. ቤተ ሰብ

ወጣቶች አባይ ነባዮችንና መናፍቃንን ከሚከተሉባቸው ምክንያቶች አንዱ:— ለጊዜውም ቢሆን የሚንከባከባቸው ቤተ ሰብ ስለሚፈልጉ ነው። የቤተ ሰብ መፍረስ፣ በወላጆችና በልጆች መካከል የማያቋርጥ ጠብ መኖር እንዲሁም አግባብ ባልሆነ መልኩ ልጆችን መቅጣት፣ ወጣቶች አዲስ ቤተሰብ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል።

በተለይ ዛሬ በርካታ አባይ ነባዮች ፕሮግራሞቻቸውን በቴሌቪዥን ማስተላለፋቸው በርካታ ወጣቶች በመርዛቸው እንዲመረዙ ምክንያት ይሆናል። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተጠናከረ የወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት ያለመኖር፣ ወጣቶች በቴሌቪዥን የሚተላለፉ የአባይ ነባዮች ፕሮግራም ትክክል ነው ብለው እንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ይችላል። መሠረታዊውን የክርስትና እምነት የማያውቁ ከሆነ፣ ትምህርቶችን የመመርመር ዐቅማቸው ደካማ ይሆናል።

### 3. ተፈላጊነትና ክበሬታን ማግኘት

ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ካጡ ወይም ቤተሰባዊነት የማይሰማቸው ከሆነ፣ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ለአባይ ነባዮችና ለመናፍቃን እንቅስቃሴ ተጋልጠዋል ማለት ነው። ምክንያቱም ተፈላጊነትን፣ ተቀባይነትንና ክበሬታን እናገኝበታለን ብለው ወደሚያስቡበት ስፍራ ሁሉ ለመሄድ አያቅማሙምና። ብዙ አባይ ነባዮች በተለይ ደግሞ መናፍቃን ተፈላጊነትን፣ ተቀባይነትንና ክበሬታን ያለገደብ እንደሚሰጡ ያውቃሉ። ታዲያ እነዚህን ነገሮች አጥብቆ ሲፈልጋቸው የነበረው ሰው በቀላሉ ይወሰዳል።

መናፍቃን ለተራው አባላቸው እንኳ የአገልግሎት ስፍራ ይሰጣሉ። ይህም የእያንዳንዱን አባል አስፈላጊነት ከፍ ያደርገዋል። ሞርሞኖች፣ "ክህነታዊ ሥራ" የሚሉትን አገልግሎት ትኩረት

ይሰጡታል። ወጣቶቻቸው የራሳቸውን ወጪ በመሸፈን የሁለት ዓመት ሚስዮናዊ አገልግሎት ያገለግላሉ። "የይሖዋ ምስክሮች" አባሎቻቸውን የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን ወንጌል ይሰብካሉ፤ ጽሑፋንም ያሠራጫሉ[10]።

## 4. አካላዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ መናፍቃን የምግባረ ሠናይን ተግባር ሲያከናውኑ ይታያሉ፤ ይኸውም የተራበን ያበላሉ፣ የታረዘን ያለብሳሉ፣ ቤተ ሰብ የሌላቸውን ልጆች በማደጎ ወስደው ያሳድጋሉ።

ለትምህርት ያላቸው ዕቅድ፣ ድርጅቶቻቸውን ለማስታወቅ የሚጠቀሙበት መንገድና ዘዴ እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀማቸው፣ ከእኛ እጅግ ብዙ ርቀው እንዲሄዱ አድርጓቸዋል። ዛሬ የመገናኛ ብዙኃንን በሰፊው እየተጠቀሙበት የሚገኙት አባይ ነባዮቹ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ብዙ መሥራት ብዙ ማሰብ ይኖርባታል[11]።

## 5. መንፈሳዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ ሰዎች አባይ ነባዮችንና መናፍቃንን የሚከተሉት መንፈሳዊ ረሃባቸውን ለማጥገብ ነው። መንፈሳዊ ረሃብ በማጥገብ ረገድ ብዙ አባይ ነባዮች የተለከፉበት፣ "የእምነት እንቅስቃሴ"

[10] እያንዳንዱ "የይሖዋ ምስክር" ይህን ሥራ ስለሚሠራ፣ "አስፋፊ" የሚል ስም ተሰጥቶታል።

[11] እያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያን በዚህ ረገድ የሠለጠነ ሰው መቅጠር የሚያስፈልገው ይመስለኛል። ከዘመኑ ጋር መዘመን ከመንፈሳዊነት የሚያጐድል ሳይሆን፣ ዘመናዊውን ሰው ባለበት አድራሻ እንዲሁም ይገባኛል በሚለው መንገድ ማግኛ ነው።



ትምህርት በዚህ ረገድ ትልቅ ቦታ የሚይዝ ነው[12]። ብዙ ወጣቶች ትምህርታቸውን ሳይመረምሩ በአምልኮ ዘያቤአቸው ተታለው ተወስደዋል፤ ይበልጡን የሚያሳዝነው የትምህርቱን ስንኩፍ ከሰሰባዎቹ ልብ ነቅሎ ለማውጣት እጅግ አዳጋች መሆኑ ነው።

አባይ ነባዮችና መናፍቃን የአነርሱን ሥርዐተ አምልኮ መከተልና ፕሮግራማቸውን በተከታታይ መካፈል፣ ለመንፈሳዊ እርካታ ዋነኛ ጉዳይ እንደ ሆነ ይናገራሉ።

## 6. ለአእምሮ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

ሰዎች በተለይም ወጣቶች መናፍቃንን የሚከተሉት ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለማግኘት ብለው ነው፤ በዚህ ረገድ "የይሖዋ ምስክሮችን" መጥቀስ እንችላለን። "የይሖዋ ምስክሮች" የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት ያለምንም ገደብና ቅድመ ሁኔታ እንደሚያምኑ ይናገራሉ። ሆኖም የግሪክና (ጽርዕ) የዕብራይስጥ ጽሑፎች እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለአስተምህሮአቸው በሚመች መልኩ አጣመው ያቀርባሉ[13]። የአቀራረባቸውም ስልት ማራኪና በኅብረ ቀለማት ያሸበረቀ ስለሆነ፣ ዕውቀት ፈላጊው ሰው በዚህ ሁኔታ በቀላሉ ይታለላል።

እንደ ቀድሞው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ዐውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲቀርቡ ያለማድረጋችን ወይም በመድረክ ውይይቶች ላይ ጠንካራ ርእሰ ጉዳዮች

[12] የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ "የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ?" በሚል ርእስ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

[13] ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን፤* ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

እንዲንሸራሸሩ ያለመፍቀዳችን እንዲሁም ወጣቶች እውነትን ከውሸት የሚለዩባቸውን የአስተሳሰብ አካሄዶች *(logic/critical thinking)* ያለማሳወቃችን በብዙ ረገድ ጉድቶናል።

ለማንበብ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች የሚመጥን፣ በተለያየ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ያለመኖሩም ወጣቶቻችን መንፈሳዊ ዕውቀታቸው ደረጃውን ጠብቆ እንዳይጐለብት እክል ፈጥሯል።

## 7. ሁለገብ የሆነ አኗኗር

አንዳንድ ሰዎች አባይ ነባዮችን እንዲሁም መናፍቃንን የሚከተሉት በአኗኗራቸው ፈጣን ለውጥ ወይም መሻሻል ስለሚያሳዩ ነው። የአባይ ነባዮች ጉባኤ በስሜት የነደደ መሆኑ፣ ወጣቶች ፈጣን የሆነ የጠባይ ለውጥ (ነገር ግን ሥር የሌለው) እንዲያሳዩ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የሲጋራ፣ የመጠጥና የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ ያለበት ሰው በአባይ ነባዮች ጉባኤና በመናፍቃን ግብረ ገብ ሊሳብ ይችላል። ምክንያቱም አባይ ነባዮች ችግርን በደቂቃ እንፈታለን ስለሚሉ እኵይ ምግባር ልማድ ሆኖ ያስቸገረው ሰው በወጥመዳቸው ውስጥ ሊገባ ይችላል። መናፍቃንም ቅድስናን አድርግና አታድርግ በሚል ቅድመ ሁኔታ ስለሚመለከቱት በእኵይ ግብረ ገብ የተቸገረ ሰው በእንዲህ ዐይነቱ የሥራ ቅድስና ትምህርት በቀላሉ ሊሳብ ይችላል።



# ክፍል ዐሥራ ሁለት

## የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን ዕድገት ለመቀነስ ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎች የትኞቹ ናቸው?



### ሀ. ሰዎች አባይ ነባዮችንና መናፍቃንን እንዳይከተሉ እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን?[1]

ሰዎች አባይ ነባዮችን ከመከተላቸው እንዲሁም መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ከመንፈቃቸው በፊት፣ ወደዚያ የሚወስዳቸውን መንገድ ማጠር ከብዙ አንጻር ጠቀሜታው እጅግ

[1] የዚህ ክፍል የሐሳቡ ጭብጥ የተወሰደው:— Alan W. Gomes, *Unmasking the Cults* (Grand Rapids: Zondervan, 1995), 86-90. ከሚባለው መጽሐፍ ነው።

ታላቅ ነው። ሰዎች በአባይ ነባዮችም ሆነ በመናፍቃን ተታለው ከመወሰዳቸው በፊት፣ ልንወስዳቸው የሚገቡ መሠረታዊ ርምጃዎች አሉ። በመሠረቱ ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን ዘዴዎች ብንጠቀም እንኳ፣ ሰዎች አባይ ነባዮችን ወይም መናፍቃንን ሊከተሉ አይችሉም ማለት አዳጋች ነው። ሰዎች መናፍቃንን እንዲከተሉ የሚያስገድዷቸውን ሁኔታዎች ማጥበብ ይቻላል፤ ነገር ግን ፈጽመን መዝጋት ወይም ማጠር አንችልም። የምንኖረው ሰይጣን በሚሠራበት፣ ሰዎች አኩይ ፍላጎታቸውን እንዳሻቸው እውን በሚያደርጉበት ዓለም ነውና።

## ለ. አባይ ነባዮችና መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለቤተ ክርስቲያን ማሳየት

### 1. ቤተ ክርስቲያን ከአባይ ነባዮችና ከመናፍቃን ልትማር ይገባታል?

መናፍቃን ሐሰተኞች ስለሆኑ፣ "ከእነርሱ የምንማረው አንዳች ነገር የለም" ብሎ ማሰብ ተላላነት ነው። መናፍቃን ሰዎችን መሳብ የቻሉት (እየሳቡም ያሉት) እውነት ባይሆንም እንኳ፣ ሰዎች የሚፈልጉት ነገር በእነርሱ ዘንድ ስላለ ነው።

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን፣ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት በቤተ ክርስቲያን ደካማ ጐኖች ላይ ስለሆነ፣ ለእነርሱ ዕድገት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በመመርመር፣ ቤተ ክርስቲያን ድካሟን አሻሽላ መቅረብ አለባት። ብዙ ሰዎች አባይ ነባዮችን ወይም መናፍቃንን የሚከተሉት በሕይወታቸው ለሚገጥማቸው ተገቢ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እስከ ሆነ ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍላጎቶች በሚመልስበት (በሚያረካበት) መልኩ ለመመለስ



መዘጋጀት አለባት። ቤተ ክርስቲያን፣ "ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ በአባይ ነባዮችና መናፍቃን ዘንድ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ያገኙት ለምንድን ነው?" ብላ ራሷን በብርቱ መጠየቅ ይገባታል። ቤተ ክርስቲያን፣ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ለሰዎች ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ልትሰማ፣ እነዚህን ጥያቄዎች ጌታ በመለሰበት መንገድ ልትመልስ ይገባታል።

ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት ተገቢ የሆነውን አእምሮአዊ፣ ማኅበራዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት እስከ ሆነ ድረስ፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍላጎቶች በሚያረካበት መንገድ በማርካት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክርስትና በቤተ ክርስቲያን ማኰልበት አለብን።

### 2. የአባሎቻችንን አእምሮአዊ ፍላጎት ማርካት አለብን

ክርስቲያን የሚያምነውን እንዲሁም ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንደሚገባው ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው ብዙ ሰዎች የሚያምኑትን ያውቁ እንጂ፣ ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንደ ተገባቸው በጭራሽ አያውቁም። እንዲያውም የበለጠ ቍጥር ያላቸው ምን እንደሚያምኑም ሆነ ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንዳስፈለጋቸው ጨርሶ አያውቁም።

ክርስቲያን በእምነት ላይ ሲተከል፣ ጸንቶም ሲቆም ይገባዋል። ማንኛውም ክርስቲያን አስተምህሮተ ሥላሴን፣ የክርስቶስን ፍጹም ሰብአዊነትና አምላካዊነት፣ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን መነሣቱን እንዲሁም ድነት በእምነት አማካይነት በጸጋ ብቻ የሚሰጥ መሆኑን ከቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ክርስቲያን በዙሪያው ያሉ አባይ

ነባዮችና መናፍቃን እዘወትረው ለሚያነሧቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ የሆነ መልስ መስጠት እለበት።

ክርስቲያን ምን እንደሚያምንና ለምን በዚህ መልኩ እንደሚያምን ከመጽሐፍ ቅዱስ መከላከያ ነጥብ ማቅረብ ካልቻለ፣ አደገኛ በሆነ መልኩ፣ ለአባይ ነባዮችና ለመናፍቃን እንቅስቃሴ የተጋለጠ ነው። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፣ "ከመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ለዘጠና ቀን የቆየ 'የይሖዋ ምስክር' መካከለኛ ዕውቀት ያለውን *(average)* ክርስቲያን በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ እምነቱን ሊያስጥለው (በእጁ ሊያስገባው) አሊያም ክፉኛ ሊያደናግረው ይችላል"። እውነት ጠልቆ የገባው አማኝ በማስረጃ ተብዬዎቹ አይሞኝም።

ክርስቲያን ከፀሓይ በታች ያሉትን የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን አስተምህሮ ሁሉ ማወቅ አያስፈልገውም። ነገር ግን ዋና ዋና እንዲሁም ተመሳሳይ ባሕርያትን ማወቅ፣ ወንጌልን ለመመስከርም ሆነ ራስን ከመናፍቃን ለመከላከል ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ስትሰጥና በአባይ ነባዮች እንዲሁም በመናፍቃን ለተጐዱት ሰዎች የማገገሚያ ትምህርት ስታስተምር [አሁን ይህም እየተረሳ እንደ መጣ ይታያል]፣ ጊዜዋንና ጉልበቷን በከንቱ ስታባክን፣ አባይ ነባዮችና መናፍቃን የብዙዎችን እምነት ሰብረው መግባታቸው ብዙ ሳያስደንቅ ይችላል።

ሰዎች እምነታችንን በተመለከተ የሚጠይቁንን አእምሮአዊ ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መመለስ ካልቻልን፣ ከባድ አጣብቂኝ ውስጥ እንደምንገባ ማወቅ አለብን። ዋቢ ይሆነን ዘንድ አንድ ምሳሌ እንጠቀም፤ አንዲት እኅት ለአንድ ሙስሊም ጐረቤቷ፣ ስለ ክርስቶስ



አዳኝነት ልትነግረው ፈለገች እንበል፤ ሙስሊሙ፣ አምላኳ እንዴት አንድ በአንጻሩ ሦስት አካል እንዳለው እንድታብራራለት ፈለገ። እርሷም፣ "ሥላሴ ልታምነው የሚገባህ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህ ትምህርት እንዲገባህ በጾም በጸሎት፣ በእግዚአብሔር ፊት ስትወድቅ እግዚአብሔር ራሱ ይገልጽልሃል" አለችው።

ከዚህ ውይይት ብዙ ነገር መመልከት ይቻላል። አንደኛው ልጆቹ የሥላሴ ትምህርት ስሜት የማይሰጥ፣ የትምህርተ መሰኮትም ሆነ የአመክንዮ መሠረት የሌለው፣ ነገር ግን ጭፍን በሆነ እምነት የሚታመን ነው ያደረገችው። ሌላው፦— "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ" *(1ጴጥ. 3፥15)* የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ አልኖረችበትም።

ቤተ ክርስቲያን ስለ አባይ ነባዮችና ስለ መናፍቃን አስተምህሮ ተግታ ማስተማር ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ቅድሚያ በመስጠት፣ የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን መሠረተ እምነት እንዲሁም የተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ምን እንደሚያምኑና ለምን በዚያ መልኩ እንደሚያምኑ ማስተማር ይገባታል። ይህም ትምህርት ክርስቲያኖች ለምስክርነት ብቁና ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ተቃውሞአቸውንም ለመመለስ የምናጠናው ጥናት፣ እምነታችንንም ሆነ ዕውቀታችንን ያጠነክረዋል።

ቤተ ክርስቲያን፣ ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ የሚረዳቸውን እንደ ሥነ አመክንዮ *(logic)* ያሉ ትምህርቶችን ልታስተምር ይገባል። ምናልባት ምን ማመን እንዳለባቸውና የትኛውን ማመን እንደሌለባቸው ማስተማር ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን

በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ከውሸት የሚለዩበትን ዘዴ ማሳወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው።

ክርስቲያን እውነትን የሚገመግምበትን፣ ሐሰትን በቀላሉ ነቅሶ የሚያወጣበትን ክሂሎት ካላገኘ፣ "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ" የሚለውን ትእዛዝ ተግባራዊ ማድረግ አይችልም።

"እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም" (ኤፌ. 4፥14)።

## 3. የአባሎቻችንን ማኅበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ማርካት አለብን

የቤተ ክርስቲያንን አባሎች መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት የቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነቶች አጠናክረን ልናስተምር ይገባል (1ጴጥ. 2፥2፤ 2ጢሞ. 3፥16)። በተጨማሪም አእምሮንና ስሜትን ሊነካ የሚችል አምልኮ መፍጠር አለብን።

አባይ ነባዮችና መናፍቃን ቅናት (zeal) አላቸው። ነገር ግን ቅናታቸው ያለ እውነተኛ ዕውቀት ነው (ሮሜ 10፥2)። በተቃራኒው እውነተኛ ክርስቲያኖች እውነትን ይዘው ሳለ ዳተኛነት ይስተዋልባቸዋል። በሚዛናዊነት የተሞላው የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ግን፣ ቅናትን ከዕውቀት ጋር ያቀናጀ ነው (2ጴጥ. 1፥3-8)።



# ሐ. አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለልጆችህ ማሳየት

## 1. ጠንካራ ቤተሰብ ልጆቹን ከሐሰተኞች በመጠበቅ ቍልፍ ሚና ይጫወታል

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በማንኛውም ጉዳይ ላይ በግልጽ መወያየትን ባህል ካደረጉ፣ መንፈሳዊውን ነገር ለመወያየት አዳጋች አይሆንባቸውም። በርግጥ ልጆች ስለተለያዩ መናፍቃንም ሆነ ሃይማኖቶች የመስማት ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን መልካም ግንኙነት ለውይይት ጥሩ መሠረት ነው።

ስለ እምነትህ ከልጆችህ ጋር በግልጽ ተወያይ። ወላጆች ልጆቻቸውን በተመለከተ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ የማስተማርም ሆነ መመሪያ የመስጠት ተቀዳሚ ኀላፊነት አለባቸው (ኤፌ. 6፥4)። ስለዚህ ተቀዳሚ ኀላፊነታቸውን በሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ትከሻ ላይ ብቻ መጣል አግባብ አይደለም። ልጆችን በእግዚአብሔር መንገድ እየመሩ ማሳደግ ቀዳሚው የወላጆች ኀላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

## 2. እንደ ማንኛውም ግለሰብ ልጆችህን አክብር

ልጆች እንደማንኛውም ግለሰብ እንዲከበሩ ይፈልጋሉ። ከወላጆቻቸውም የተለየ ማንነት አላቸው። ወላጆች ልጆቻቸው ማንነታቸውን ሲገልጹ የሚፈልጉበትን ተገቢውን ነጻነት ሊነፍጓቸው አይገባም። ልጆች ይህን የሚያጡ ከሆነ፣ ወደ አባይ ነባዮችና መናፍቃን እንዲሄዱ ሊገፋፉ ይችላሉ። አባይ ነባዮችንና መናፍቃንን በመከተል ከቤተሰቦቻቸው የተለየ ማንነት እንዳላቸውና የተለየ የአኗኗር ዘይቤ እንደሚከተሉ ማሳያ መንገድ አድርገው ሊጠቀሙበት

ይችላሉ። የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንንም የአኗኗር ዘይቤ በመከተል፣ ራሳቸውን ከቤተሰቦቻቸው ሲለዩ ይችላሉ።

ብልኀ ወላጆች የልጆቻቸውን ማንነት መግለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ለምሳሌ እንደ አለባበስ፣ እንደ አበጣጠር ወዘተ… ያሉትን እንዲያደርጉ ይፈቅዱላቸዋል። በነገር ሁሉ ስኬታማ የሚሆኑበትን መንገድ ያመቻቻሉ። ብዙ አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ የስኬታማነትን አጭር መንገድ እናሳያለን ስለሚሉ፣ ልጆች በዚህ ቀንበር ተጠምደው ሊከተሏቸው ይችላሉ።

## 3. የልጆችህን ጥያቄ በአንክሮ ልትመለከተው፣ አጥጋቢ መልስም ልትፈልግለት ይገባል

አንዳንድ ልጆች ስመንፈሳዊ ጥያቄዎቻቸው መልስ ፍለጋ መናፍቃንን ሊከተሉ ይችላሉ። ልጆች ጥያቄዎቻቸው በአጥጋቢ ሁኔታ ካልተመለሰ፣ ጥያቄአቸውን ሊመልሉ ወደሚችሉ መልስ ሰጪዎቻቸው አምነትና የአኗኗር ዘዴ መሄዳቸው አይቀሬ ነው። ልጆች ከባድ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ እንኳ ቢጠይቁ፣ ወላጆች የጥያቄውን መልስ ለማግኘት መጣር ወይም በበቂ ሁኔታ ሊመልሱላቸው ወደሚችል ሰው ዘንድ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል[2]።

ልጆች አስደንጋጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጥያቄዎችን እንኳ ቢጠይቁ ልንቈጣቸውም ሆነ ልናስደነግጣቸው ፈጽሞ አይገባም።

[2] በዚህ ረገድ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ የሚከተሉትን ሦስት መጻሕፍት ለንባብ አቅርቧል:— *እግዚአብሔርን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 101 ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው* (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ 1992)። *መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 102 ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው* (ቃለ ሕይወት፤ 1993)። *ትክክልና ስሕተትን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 103 ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው* (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ 1992)።



እግዚአብሔር የት ነው የሚኖረው? እርሱን ራሱን ማን ፈጠረው? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በምን ዐውቃለሁ? ውሸት ለምን ትክክል አልሆነም? ወዘተ የሚል ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ነገር ግን ከምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በጣም የከፋው፣ ልጆችን ማስደንገጥና ጥያቄዎቻቸውን ማጣጣል ነው።

ወጣቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ የሚያስቡበትን ነገረ መለኮታዊና ሥነ አመክንዮአዊ አካሄዶችን ልናስተምራቸው ይገባል።

## 4. ከልጆችህ ጋር ወጥነት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ ኑር

ልጆች ግብዝነትን ከሩቅ ነቅሰው የማውጣት አስመሳይነትን የመለየት ታላቅ ችሎታ አላቸው። ወጥነት ያለውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ከልጆችህ ጋር በጋራ የማትኖር ከሆነ፣ ልጆችህ ክርስትናን ቢያወግዙ አትደነቅ!

ወጥነት ማለት ፍጹምነት ማለት አይደለም። ነገር ግን ወጥነት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ ማለት፣ ክርስትናን የአኗኗራችን፣ የአስተሳሰባችንና የአነጋገራችን መሠረት ማድረግ ማለት ነው። ልጆች ችግርን እንዴት እንደምትፈታ ካንተው ከአባታቸው[3] ሊማሩ ይገባል። ለምሳሌ:— ልጆችህ ሲበድሉህ ወይም ሲያጠፉ ለእነርሱ ያለህ ይቅርታ፣ አንተም ስታጠፋ ጥፋትህን በግልጽ በማመን የምትጠይቀው ይቅርታ ለልጆችህ መልካም አርአያ፣ ጥሩም ምሳሌ

[3] በርእሱ ላይ የተባእት ጾታን ስለተጠቀምን፣ በዚህ ቦታ "አባት" የሚለውን ቃል ተጠቅመናል። አባትና እናትን በተለዋዋጭነት ማቅረብ፣ የአሳብ ፍሰቱን የደናቅፋል ብለን ስላሰብን፣ አንዱን ብቻ ነጥለን ተጠቅመናል። ስለዚህ እናቶች "እናት" የሚለውን እየተኩ እንዲያነቡ በማክበር ይጠየቃሉ።

እንደሚሆናቸው እሙን ነው። ይህም የእምነትህን እውነተኛነት በኀይል ያገልጠዋል።

## ፭. ልጆች እውነታዎችን የሚመዝኑበት ጥሩ ዘዴ ስጣቸው

ልጆች እውነቱን ከውሸት ሊለዩ የሚችሉበትን ዘዴ ስጣቸው (አስተምራቸው)። ዘዴዎች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ከውሸት ልንለይ የምንችልባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ምንም እንኳ በእያንዳንዱ እስተምህሮ ሐሰቱንና እውነቱን ጠልቀን ባናስተምራቸውም፣ በሚገጥሟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የሚረዱአቸውን ዘዴዎች ማስተማር በቂ ነው። ዘዴዎች ማንኛውንም ነገር የምንመዝንባቸው መሣሪያዎች ናቸውና።



# ክፍል ዐሥራ ሦስት

## ጸረ-ተምህሮታዊነት
## የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት
## አብሾ፣ እርሾና ጌሾ



ከአሜሪካን መሥራች አባቶች መኻል አንዱ የሆኑት ቤንጃሚን ፍራንክሊን፣ "ሃያ ስድስት ወታደሮች ስጡኝ ዓለምን በቍጥጥሬ ሥር አደርጋለሁ" ይሉ እንደ ነበር ይነገራል። ግለሰቡ ሃያ ስድስት ወታደር የሚሏቸው በወታደራዊ ሳይንስ የሠለጠኑ፣ በጦር ዐውድማ የተፈተኑ፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቁ፣ በጦር ፍልስፍና

የመጠቁ ሾተላይ ወታደሮችን አይደለም:: በእንግሊዝኛ የፊደል ገበታ ላይ የተለተሩትን፣ ሃያ ለድስት የእንግሊዝኛ ሆህያት እንጂ[1]::

የግእዝ ቋንቋ ሊቃውንት፣ ሰዎች "ነባብያን ወንቁኀን" ናቸው ሲሉ፣ የኀልዩ የነቢብና የገቢር (የአስተላለብ፣ የንግግር እንዲሁም የምግባር) ባለህብት መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ የሥነ ጽሑፍ ባለቤት መሆናቸውንም የሚያመለክት ነው:: እርግጥ ነው፣ የሥነ ጽሑፍን ኀያል ጉልበት፣ ሥነ ጽሑፍ ራሱ ነግሮ ዘክሮ እንደ ማያጨርሰው እናውቃለን:: ምክንያቱም ዕውቀትን ከአንድ ጭንቅላት ወደ ሌላ አእምሮ የምናስተላልፍበት (የምናንቈረቊርበት) ሁነኛ ቦይ ሥነ ጽሑፍ ነው::

ኮሚኒስቶች የፖለቲካና የምጣኔ ሀብት ርእዮተ ዓለማቸውን በዓለም ላይ እንዲናኝ ያደረጉት፣ በሰላ ብዕራቸው፣ በቀስቃሽ ጽሑፋቸው ነበር:: በዚህ ረገድ፣ በዘመነ ደርግ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጕመው ለንባብ የቀረቡትን የካርል ማርክስን ዳስ ካፒታልና ኮሚኒስት ማኒፌስቶ መጻሕፍት ያስተውሷል:: በ"ቀዝቃዛው ጦርነት" ወቅት፣ በርካታ አገሮች ከኮሚኒስቷ መስኮብ/ራሻ ተርታ መሰለፍ የቻሉት፣ የርእዮተ ዓለሙ መሪዎች ፍልስፍናቸውን ለአእምሮ ግቡዕ በሆነ ሁኔታ በሥነ ጽሑፍ ከሽነው በማቅረባቸው ነበር::

በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው የፕሮቴስታንቱ የተሐድሶ እንቅስቃሴ፣ እንደ ምትሐት ሊታይ የሚችል ነውጥ ማስከተል የቻለው፣ ንቅናቄው ትምህርትን ማዕከል እንዲሁም ሥነ ጽሑፍ መር የመሆኑ ሐቅ ነው:: የማኅበረሰብን አኗኗርና ለውጥ ይከታተሉ የነበሩ የዘመኑ ደራስያን፣ "የፕሮቴስታንት ተሐድሶን በማይጠፋ እሳት በነዳጅ ያንቀለቀለው፣ የኅትመት መሣሪያ ፈጣሪው ጀርመናዊው ዮሐንስ ጉተንበርግ ነው"

[1] ከወንድም ምኒልክ አስፋው ያገኘሁት ነው::



ሲሉ ጽፈዋል:: ከንቅናቄው ቀደም ብሎ ዮሐንስ ጉተንበርግ የማተሚያ መሣሪያ ባይፈጥር ኖሮ፣ የሉተርና የመርሕያነ ተሐድሶዎች ጥረት፣ ከመንደር ጫጫታ ዘለግ ያለ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም ነበር::

አትንቀስም አትገሠሥም በተባለችው ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የተኰለኰሉት አውሮፓውያኑ ነገሥታት፣ በዐይን ብሌን የሚመስሉትን ካቶሊካዊት እምነታቸውን ከጥቃት የመከላከል ዐቅም ያጡት፣ ከእነርሱ ጉልበት የሚበረታ ኀይል እንደ ደራሽ ውሃ ድንገት ከተፍ በማለት፣ በእርዳ ተራዳ የቆመውን ነገር ግን ሐዳስያኑ በለላ ሒስ የሞሸለቁትን ተረት፣ ዳግም በእግሩ ማቆም ባለመቻላቸው ነበር:: አስደናቂው ነገር፣ እንደ ሰሚ ሁሉ በነገረ መለኮቷም፣ "ዓለም ዐቀፋዊት ነኝ" ብላ ትከራራ የነበረችው ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን፣ በመራሕያነ ተሐድሶዎቹ የዕድሜ ዘመን እንኳ፣ ሊጠገን በማይችል ደረጃ በግማሽ መሰንጠቋ፣ የትምህርትንና የሥነ ጽሑፍን ጉልበት በውል የሚያሳይ ጥሩ ማገናዘቢያ ይመስለኛል::

ከዐሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ ከአውሮፓ እንዲሁም ከሰሜን አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሚስዮናውያን፣ ወንጌልን ለመስበክ በሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ስብከተ ወንጌልና የቀለም ትምህርትን እንደ ነበልባልና እንደ ብርሃን እያያዘውት ዘልቀዋል:: ቀደምት ኢትዮጵያውያን ምሁራን፣ ፊደል በመቊጠር በዘመናዊው ትምህርት መሟሸት የጀመሩት፣ በሚስዮናውያኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውስጥ እንደ ሆነ ይታወቃል:: የቀለም ተቀብያ አላቸው ያሏቸውንም የበለጠ ትምህርት ያገኙ ዘንድ ከአገር ውጪ ሄደው እንዲማሩ ብዙ ጥረት አድርገዋል:: በዚህ አግባብ ነበር አንድ ሰው፣ "ተቀመጥ በወንበሬ ተናገር በከንፈሬ" በሚል

በሚስዮናውያኑ ትምህርት ቤት ይሄም የነበረው (እኔም በአብዛኛው የትምህርት ዕድል ያገኘሁት በዚሁ አካሄድ ነው)፡፡

ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ፣ ከዘመነ ተሐድሶ ጀምሮ ለረጅም ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍን ለአምስት ዐበይት ዐላማዎች ስትጠቀምበት የመኖሯ ሐቅ ነው፡፡ ይኸውም፡— (1) መሠረተ እምነቷን ከጥቃት ለመጠበቅ፣ (2) ተጻራሪ አስተሳሰቦችን ለማምከን፣ (3) ወንጌልን ለማሠራጨት፣ (4) አባሎችዋን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርትና በክርስቲያናዊው ንጽርአተ ዓለም ለማነጽ እንዲሁም፣ (5) አምልኮተ እግዚአብሔር ለማካሄድ፡፡

ይህ ግን የነበረ እንጂ አሁን ያለ ሐቅ አይደለም፡፡ ዕውቀትና ሥነ ጽሑፍ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕይወት እየመነነ፣ ከዐውደ ምሕረቱ እየበነነ የባዕድ አገር ሰው እንደ ሆነ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም ቅዱሳት መጻሕፍትን ደርዝ ባለው መልክ መተንተን፣ "የአእምሮ ሰው" ወይም "የቃል ሰው" የሚል አሉታዊ ስያሜ የሚያከናንብ ሲሆን፣ ከዚህ በተቃራኒው አንጻር የቆሙትን ግን፣ "የጸጋ አገልጋዮች" "መንፈሳውያን ሰዎች" የሚል ትልቅ ክብር ያጐናጽፋል፡፡ ይህ መቼም ሥነ ጽሑፍ ታሽቶ ባደገበት አገር በዚህ መጠን ምጽአተኛ ሲሆን ማየት፣ በርግጥም ትልቅ ቊጭት የሚፈጥር ነው፡፡

## የሰምና ወርቁ ማዕቀፍ

ወደድንም ጠላንም በኢትዮጵያ ውስጥ የተነሣው የአባይ ነባዮች እንቅስቃሴ፣ ክርስቲያኖች ቃለ እግዚአብሔርንና ምርምርን የጐዞ መስመራቸው እንዳያደርጉ እጅግ ትልቅ አክል ፈጥሮአል፡፡ ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ እንዳብራራ ይፈቀድልኝ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ትልቅ ትዕግሥትና ብዙ ትግል ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ



በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መኻል ተዘውትረው የሚጠቀሱትን ሦስት መሠረታውያን ነጥቦች ልጥቀስ፡— (1) መጽሐፉ ጥንታዊ መሆኑ አንብቦ የመረዳቱን ሥራ አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በእኛና በመጽሐፍ ቅዱስ ቀዳማይ ተደራስያን መኻል፣ የብዙ ሺህ ዓመት ርቀት አለ፡፡ ብሉያት ከሦስት ሺህ ዓመት በፊት የተጻፉ ሲሆን፣ ሐዲሳት ደግሞ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ነው የተጻፉት፡፡ ይህ ደግሞ በእኛና በቀዳማይ ተደራስያኑ መኻል ያለውን ንጽሮተ ዓለም በከፍተኛ ደረጃ አለያይቶታል፡፡ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የፍልስፍና ወዘተ ምጥቀት የዘመኑን ሰው አመለካከት ከጥንታውያኑ ሰዎች አተያይ በከፍተኛ መጠን አራርቆታል፡፡ (2) በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፍያንና በመልእክቱ ቀዳማይ ተደራስያን መካከል ከፍተኛ የሆነ የባህል ልዩነት አለ፡፡ ይህም ተግባቦቱ እንዲደነቃቀፍ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ (3) መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ እኛ ከምናውቀው ቋንቋ፣ ዘይቤአዊ አገላለጽ፣ ሥነ ጽሑፋዊ ዘውግ፣ ወዘተ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡

ይህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ በትክክል ለመረዳት ረጅም ጊዜ የሚፈጅ እልህ አስጨራሽ ትግል ፈልጓል፡፡ አምላክ አሳቡን ለሰብአውያን ለማስተላለፍ፣ ይህ ዐይነቱን አድካሚ መንገድ ለምን እንደ መረጠ እኔ የማውቀው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡ ይኸውም አምላክ ቅዱሱን መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ ነድቶ እንካችሁ እንዳለን ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ ይህን የመረዳት ክፍተት የሚሞሉልንን አስተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቶአል፡፡ እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለረጅም ዓመት በማጥናት ክፍተቱን ለመሙላት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፤ በየቋንቋውም ተርጕመው አቅርበውልናል፡፡ ይህ ሁሉ እውን ቢሆንም እንኳ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ መረዳት ትልቅ ጥረት ይፈልጋል፡፡

ሥነ አፈታትን ማወቅ፣ እናት ቋንቋውን ማወቅ፣ ነገረ መለኮትን ማወቅ፣ ወዘተ። ስለዚህ አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ የእምላክን ምክር ለመረዳት ከእነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ጋር መፋጠጡ አይቀሬ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ያስፈለገበት ዐቢይ ዐላማ፣ አምላክ በግልም ሆነ በጋራ የሚናገረንን ነገር በግልጽ ለመረዳት ነው። የትንቢትም ዋነኛ ዐላማ ይኸው ነው። በተወሰኑ አጋጣሚዎች ውስጥ ዐልፎ ዐልፎ እግዚአብሔር ነቢያትን በማስነሣት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለቤተ ክርስቲያን ምሪትን ይሰጣል። ከላይ እንደ ተመለከትነው ይህ በብሉያትም በሐዲሳትም የነበረ ዛሬም ያለ ቋሚ አካሄድ ነው። ነገር ግን አምላክ የየዕለቱን ትምህርትና ምክር የሚሰጠን በቅዱሳት መጻሕፍት እንጂ በነቢያት አይደለም፤ አልነበረምም።

ዛሬ በዙሪያችን እንደ እንጉዳይ የፈሉት አባይ ነባዮች፣ ቢያስፈልግ በቀን ዐሥር ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ ላይ አምላከ ሊናገረን የሚፈልገውን ነገር ንገሩን ብንላቸው ይነግሩናል። እንግዲያው አምላከ በነባዮች በዚህን ያህል ቅርበትና በዚህን ያህል መጠን የሚናገረን ከሆነ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማጥናት በተለይ ደግሞ ከዚህ ጥንታዊ መጽሐፍ ጋር መታገል ለምን ያስፈልጋል? ይህ ነው የማንበብ ፍላጎታችንን ያሰለሰው፤ የሰለበው! ይህ አካሄድ ነው መጽሐፍ ቅዱሳችንን ያስረጀብን!

አንድ ወዳጄን፣ “ጌታ በዚህ መጠን በነባዮች የሚናገረን ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊነቱ እምኑ ላይ ነው?” አልሁት። እርሱም በኵራት፣ “ሁል ጊዜ  አንድ ዐይነት ወጥ ብቻ እንዴት ትበላለህ? ይሰለቻል እኮ!...መገለጥና ትንቢት ጥቍሩ መጽሐፍ እንዳይሰለቸን አምላክ የሰጠን ተለዋጭ ወጥ፣ ያውም የዶሮ ወጥ



ነው” አለኝ። “‘በጥቍሩ መጽሐፍና’ ‘በዶሮው ወጡ’ መኻል በመዳኘት፣ ሚዛናዊ ክርስትናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንመሠርተው እንዴት ነው?” የሚለው ጥያቄ እጅግ ወሳኝ፣ እጅግም አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። ለዚህ ሁነኛ ጥያቄ ሁነኛ መልስ ሳንሰጥ ፊታችንን እነርሱ “ጥቍሩ መጽሐፍ” ወደሚሉት እንመልሳለን ማለት ከቀቢፀ ተስፋ[2] ነው፤ ከንቱ ተምኔት ነው። ይህ ለዘመኗ ቤተ ክርስቲያን የቀረበ ወሳኝ ጥያቄ ነው።

ቀጥለን የማንበብ ባህላችን ምንኛ እንደ ተንኰታኰተ በግልጽ ሊያሳየን እንዲሁም ሊያገናዝብልን የሚችል አንድ ማነጻጸሪያ በናሙናነት ወስደን እንመልከት። ይህ በምን መጠን ተኽረብርበን እንደ ወደቅን በጉልኅ ያሳያል ብዬ አስባለሁ። እነሆ:—

ለዚህ ጉዳይ የመረጥሁት የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀውን “የይሖዋ ምስክሮችን” ድርጅት ነው። የእነርሱ ትጋት ለእኛ ሥጋት፣ የእነርሱ ጥረት ለእኛ ኀፍረት፣ የእነርሱ ከፍታ ለእኛ ዝቅታ ሊሆን እንዴት እንደ ቻለ እንመርምር።

## ማገናዘቢያ

## ሀ. ኅትመትና ሥርጭት

ከማንኛውም መናፍቃን ይልቅ የጽሑፍ ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ በመጠቀም ላይ የሚገኙት፣ “የይሖዋ ምስክሮች” ናቸው። ከ26 ዓመት በፊት ይፋ የሆነ አንድ መረጃ፣ “የይሖዋ ምስክሮች” በዓለም ዙሪያ 33 ታላላቅ ማተሚያ ቤቶች እንዳላቸው ይገልጻል። “ቤቴል” በመባል የሚታወቀው ትልቁ ማተሚያ ቤታቸው ብቻ፣ በቀን

[2] “ቀበፀ” ማለት ቈረጠ ነው። ስለዚህ “ቀቢፀ ተስፋ” ማለት ተስፋ መቍረጥ ማለት ነው።

ርዝመቱ 1,000 ማይል (1,609 ኪሎ ሜትር) የሚያህል ወይም 61 ሚልዮን ገጽ ወረቀት ያትማል[3]:: ከዚህ በተጨማሪ በወር 3 ሚሊዮን የአዲሲቱን ዓስም ትርጉም እያተመ ያወጣል። በ1991 ዓ.ም. በእነዚህ ማተሚያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ 11,000 የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ነበሩ[4]::

እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን ቀመር 2013 ዓ.ም "የይሖዋ ምስክሮች" ጽሑፎቻቸውን 700 ቋንቋዎች በመተርጐም 239 አገሮች ውስጥ አሠራጭተዋል[5]:: ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ተደርጐ የተተረጐመው የአዲስ ዓስም ትርጉም በ2013 ዓ.ም ብቻ፣ በ121 ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ 184 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[6]::

ሁሰቱ የድርጅቱ ዕውቅ መጽሔቶች ማለትም፡ "መጠበቂያ ግንብ" እና "ንቁ" መጽሔት የኅትመት ብዛታቸው፣ የሥርጭት ስፋታቸው እንዲሁም የሚተረጐሙበት የቋንቋ ብዛት በርግጥ እንደ ትንግርት ሲታይ በሚችል ደረጃ ላይ ይገኛል። ሰምሳሌ 2013 ዓ.ም "መጠበቂያ ግንብ" 210 ቋንቋዎች በመተርጐም 45 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[7]:: "ንቁ" መጽሔት ደግሞ፣ በ99 ቋንቋዎች የተተረጐመ ሲሆን፣ 44 ሚልዮን ቅጅ ታትሞ ተሠራጭቷል[8]:: ሥርጭቱም ሪደርስ ዳጀስት እንዲሁም ቲቪ ጋይድ ከሚባሉት መጽሔቶች ካላቸው ሥርጭት ጋር የሚስተካከል፤ ሽያጩም ከታይምስ፣ ከኒውስ ዊክ፣ ከዩ ኤስ ኒውስና፣ የወርልድ ሪፖርት ጋር የሚወዳደር ነው[9]::

የአዲሲቱ ዓስም ትርጉም በ1990 ዓ.ም ብቻ በ67 ሚልዮን ቅጂዎች የተባዛ ሲሆን፣ በ14 ቋንቋዎች ተባዝቶ ስንባብ ቀርቧል። በአሁኑ ጊዜ ይህ መጽሐፍ አማርኛን ጨምሮ ከ129 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል[10]::

ይህ የድርጅቱ መጽሔቶች ልዩ ጠባይ ብቻ አይደለም። የመጻሕፍትና የመስስተኛ መጻሕፍት *(brochure)* ነባር ባሕርይ ጭምር አንጂ። ስምሳሌ፣ "ትክክስኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው?" በሚል ርእስ የታተመውና የድርጅቱን መሠረተ እምነት ለአዳዲስ ተከታዮች የማስተማሪያ መጽሐፍ (224 ገጽ አሰው)፣ ስመጀመሪያ ጊዜ ስንባብ የበቃው በ2005 ዓ.ም ሲሆን፣ 240 ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ 214 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[11]::

በቅርቡ፣ "አምላክን ስማ የዘላስም ሕይወት ታገኛስህ" በሚል ርእስ የተዘጋጀው ባስ 32 ገጽ ጥራዝ መስስተኛ መጽሐፍ 400 ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ በ42 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[12]::

በ2012 ዓ.ም ብቻ በድርጅቱ ማተሚያ ቤቶች የታተሙት መጽሔቶች ብዛታቸው 1.3 ቢሊዮን ሲሆን፣ መጽሐፍ ደግሞ 80 ሚልዮን ነው[13]::

---

[3] *CRI "Cult Growth Statistics", Citing the Watchtower (1, Jan.1993): 19b.*

[4] *David A. Reed, Jehovah's Withness Litrature: a Critical Guide to Watchtower Publications (Grand Rapids:Baker, 1993), 9.*

[5] *https://www.jw.org/en/jehovahs-witnesses/activities/publishing/global-printing/*

[6] ዝኒ ከማሁ።

[7] ዝኒ ከማሁ።

[8] ዝኒ ከማሁ።



---

[9] *Alan W.Gomes, Unmasking the Cults, 23.*

[10] *https://www.jw.org/en/publications/books/2016-yearbook/highlights/new-world-translation-more-languages/*

[11] *https://www.jw.org/en/jehovahs-witnesses/activities/publishing/watchtower-awake-magazine/*

[12] ዝኒ ከማሁ።

[13] ዝኒ ከማሁ።

ኅዳር 1 ቀን 2005 ዓ.ም ለንባብ የበቃው፣ "የመጠበቂያ ግንብ" መጽሔት፣ በገጽ 27 ላይ ድርጅቱ አዘጋጅቶ ያሠራጫቸውን የኅትመትና የቪዲዮ ውጤቶች በሚከተለው መልክ ይፋ አድርጓል።

- 3,168,611 ቪዲዮዎች
- 6,834,740 መለስተኛ መጻሕፍት
- 47,490,247 መጻሕፍት
- 167,854,462 በአንድ ርእስ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥኑ ብሮሹሮች
- 440,995,740 በራሪ ክጽሑፎች
- 1,179,266,348 (1.2 ቢሊዮን የሚጠጋ መጽሔት)

በኅትመት ብዛት ብቻ ሳይሆን በሥርጭትም ብዛት እንዲሁም በሚተረጐሙባቸው ቋንቋዎች ብዛት የድርጅቱ መጽሔቶች እንዲሁም መጻሕፍት በዓለም የቍጥር አንድ ቦታን ይዘዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ድርጅቱ በብዛት ብቻ ሳይሆን፣ በዐይነትም እጅግ በርካታ መጻሕፍትን ዐትሞ በማሠራጨት ላይ ይገኛል። የኅትመት ጥራታቸው እጅግ የላቀ እንዲሁም በሙሉ ቀለም የታተሙ በመሆናቸው፣ የማንበብን ፍላጎት ይቀሰቅሳሉ። ከዚህ በተጨማሪ የኅትመት ውበታቸው እምሮና ደምቆ መቅረቡ፣ እንባቢው የያዙትም ትምህርት ትክክል ነው የሚለውን፣ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ አድርገዋል። ይህ ደግሞ ድርጅቱ ለዘመናት ሲጠቀምበት የኖረው ስልት ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተዘጋጁ ያሉት መጻሕፍት፣ በምን ያህል ቍጥር ተባዝተው እንደ ተሠራጩ በቍርጥ ማወቅ አልተቻለም። ከዚህ በፊት ግን በመጻሕፍቱ መግቢያ ላይ፣ በምን ያህል ቍጥር ታትሞ እንደ ተሠራጨ ይገልጽ ነበር።



ከዐሥር ዓመት ወዲህ በአማርኛ ቋንቋ የታተሙት መጻሕፍት ወደ 35 ይደርሳሉ (በጣት የሚቈጠሩ የቀድሞዎቹን ጽሑፎች ሳይጨምር)። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:— "ቅዱሳት መጻሕፍትን በየዕለቱ መርምር"፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምራል?"፣ "ምን ጊዜም ለይሖዋ ታማኝ ሁኑ"፣ "የምርምር መርጃ መሣሪያ ለይሖዋ ምስክሮች" (የ2015 ዕትም)፣ "ወደ ይሖዋ ተመለስ"፣ "ኢየሱስ—መንገድ እውነት፣ ሕይወት"፣ "የእምላክ መንግሥት እየገዛ ነው"፣ "የእምላክ ወዳጅ መሆን ትችላለህ"፣ "የምትወዱት ሰው ሲሞት"፣ "ልጆቻችሁን አስተምሩ"፣ "ደስተኛ ቤተሰብ ሊኖርህ ይችላል"፣ "የእምላክ መንግሥት ምንድን ነው?"፣ "ለይሖዋ ዘምሩ"፣ "በእምነታቸው ምሰሏቸው"፣ "መከራ የማይኖርበት ጊዜ ይመጣል?"፣ "የቤተሰብን ሕይወት አስደሳች ለማድረግ ቍልፉ ምንድን ነው?"፣ "ዓለምን እየተቈጣጠረ ያለው ማን ነው?"፣ "ስለ ወደ ፊቱ ጊዜ ምን ይሰማሃል?"፣ "ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን አመለካከት አለህ?"፣ "የሞቱ ሰዎች እንደ ገና በሕይወት መኖር ይችላሉ?"፣ "ወጣቶች—በሕይወታችሁ ምን ማድረግ አስባችኋል?"፣ "ከእምላክ ፍቅር አትውጡ"፣ "ወደ ይሖዋ ቅረብ"፣ "ከታላቁ አስተማሪ ተማር"፣ "ስለ እምላክ መንግሥት የተሟላ ምስክርነት መስጠት"፣ "በቲኦክራሲያዊ የአገልግሎት ትምህርት ቤት ከሚሰጠው ሥልጠና ተጠቀም"፣ "ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው?"፣ "መጽሐፍ ቅዱስ—የያዘው መልእክት ምንድን ነው?"፣ "እምላክን ስማ"፣ "እውነቱን ማወቅ ትፈልጋለህ?"፣ "ሕይወት የተገኘው በፍጥረት ነው?"፣ "የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች መማሪያ መጽሐፍ"።

## የአባላት ብዛት

